# ለአዲስ ዴሞክራሲያዊ ጅማሮ



የኢትዮጵያ ህዝቦች ከጭቆና አገዛዝ ተላቀው ወደሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመሸጋገር የነበራቸው ህልም ከታሪክም ሆነ ከአካባቢው ዓለም ምንም የረባ ትምህርት መቅሰም ባልተሳካላቸው አብሪተኛ መሪዎቻቸና በባእድ ኃያላን አውር ወገናዊነት ተገግዞ፣ 30 ዓመታት በማይሞላው ዘመን ለሶስተኛ ጊዜ በመክሰም ላይ ይገኛል::

የዛሬ አራት ዓመት የደርግ አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ትግል ሲገዘገዝ ቆይቶ ሲንኮታኮት፣ በጦር ሜዳ ባበለፈው ኃይል ብቻ ሳይሆን በቀርበና በሩቅ ባእዳን ኃይሎች የማቴር ያል፣ የፋይናንስና የዲፕሎማሲ ድጋፍ ኢህአዴግ የመንግሥት ሥልጣን ሲጨብጥ ህልማቸንና ተስፋቸን የአዲስ ጅማሮ ህልምና ተስፋ ነበር::

የሽግግሩ ዘመን ይህንን ታሪካዊ ተልእኮውን ሳይፈጽም፣ ህብረተሰባቸንን እንዳለ ከጸረ ዲሞክራሲያዊ ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሳይሆን አንድን አናሳ ኃይል ከጊዜያዊ የሥልጣን ባለቤትነት ወደዘላቂ ፈላጭ ቆራጭነት አሸጋገሮ በመክሰም ላይ ይገኛል:: "ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ተካሄደ፣ ሃገሪቱ ዲሞክራሲያዊ የሆነ ህገ መንግሥት ተጎናጸፈች" እየተባለ በማንም ሆነ በማንም ቢለፈፍ ይህንን መራራ ሃቅ የሚሸር ነገር የለም::

የሃገራችንን ችግሮች በሰላማዊ ዘዴ ፈትተን ህብረተሰባችንን የዲሞክራሲ፣ የሰላማትና የብልጽግና ጉዳና ለማስያዝ ምርጫና ህገ መንግሥት እያሉ መለፈፉ በምንም ዓይነት በቂ ሊሆን እንደማይቻል ባለፈት 65 ዓመታት በዚሁ ጉዳይ ያየናቸውና የሰማናቸው ክስተቶች በቂ ማስረጃ ይመስሉናል::

በነዚሁ ሁሉ ዓመታት ከአጼ ኃይለሥላሴ እስከኢህአዴግ ያየናቸው በገዥዎች ሙሉ ቁጥጥር ሥር የተካሄዱ የሸፍጥ ምርጫዎች ነበሩ:: እነዚሁ ምርጫዎች የተካሄዱባቸው ህገመንግሥታዊ ክለሎች የገዥዎችን ፖለቲካና ርእዮተዓለም የሚያንጸባርቁና የረባ ሰላማዊ ለውጥ ሂደት በር የሚዘጉ ስለነበሩ ለሃገራችን ችግሮች መፍትሄ የሚጠቁሙ አልነበሩም:: ምርጫ ተደርጉ በሥልጣን ላይ ያለ መንግሥት ወርደ በሌላ የተተካበት ዘመን በታሪካችን አላየንም:: ህገ መንግሥት ተብሉ ገዥዎችም ተገዥዎችም በእኩል የሚያከብሩት ሰነድ በታሪካችን እስከዛሬ አላየንም::

በዚህም የተነሳ በሃገራችን ለዲሞክራሲ፣ ለብሄራዊ ክብርና ነጻነት፣ ለብሄሮች ብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት፣ ለማህበራዊ ፍትህና ለሰላም የሚታገሉ ኃይሎች የሰላማዊ ለውጥ በሮች በላተዘጉባቸው የአመጽ ጉዳናን ለመከተል ሲገደዱ አይተናል:: የተፈራረቁብንን አገዛዞች በሰላማዊ ዘዴ ለመቋቋም የተነሱ ኃይሎች ደግሞ በገዥዎች አብሪት ለእሥራት፣ ለአፈና፣ ለግድያና ለስደት መከራ ሲዳረጉ ቆይተዋል:: በመሃል አገራችን ለዘመናት ሲያዋክቧት በኖሩት አመጸና አለመረጋጋት የተነሳ የችግር፣ የርሃብ፣ የኃላ ቀርነት ... ሆና፣ ኢኮኖሚዋ ደቆ፣ ማህበራዊ ኑሮዋ ተናግቶ ዛሬ የምትገኝበት አሳዛኝ ሁኔታ ላይ ወድቃለች::

ከአጼ ኃይለሥላሴ እስከኢህአዴግ ዘመን ምርጫና ህገ መንግሥት ለሃገራችን ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት ያልቻሉበት ምክንያት ግልጽ ይመስለናል:: የፍሬቢስነታቸው ዋናና መሠረታዊ ምክንያት ከምርጫና ህገመንግሥት ቀድሞ በሃገሪቱ ለዲሞክራሲ የተመቻቸ የፖለቲካ አካባቢ ባለመኖሩ ነው:: በዚህ ጸረ ዲሞክራሲያዊ አካባቢ የገዥዎች ሙሉ ቁጥጥር ሥር የተካሄዱ ምርጫዎች እንደማንኛውም ነጻ ምርጫ "ያለን መንግሥት ለተወሰነ ተጨማሪ ጊዜ ለማቆየት ወይም ደግሞ እሱን ቀይሮ ሌላ መንግሥት ለመሰየም" ታስበው የተዘጋጁ ምርጫዎች አልነበሩም:: የተካሄዱትም የረባ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ለውጥ በማይፈቅዱ ህገ መንግሥታዊ ክለል ውስጥ ነበር::

አሁንም አንደተላንቱ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች ባልተከበሩበት ሁኔታ ስለ ነጻ ምርጫና ዲሞክራሲ ይለፈፋል:: ዱፍን ዓለም የተቀበላቸውን የነጻ ምርጫ መርሆዎች ረግጦ በተሰናዳና በተካሄደ ምርጫ አማካኝነት የህዝብ ፈቃድ ተብሎ የህዝቦችን መብት በምንም ዓይነት የማያረጋግጥ፣ የገዢዎችን ሥልጣን በምንም ሁኔታ የማይገታ ህገ መንግሥት ተመልሶ ተጭናብናል:: አሁንም አንደተላንቱ የአንዱን አናሳ ኃይል ርእዮተዓለምና የፖለቲካ አቋም፣ የኢኮኖሚና የበሸለ ፖሊሲ የሚያንጸባርቅ ሰነድ የሃገሪቱ የበላይ ህግ ተብሎ የኢትዮጵያ ህዝቦች የሰላምና የዲሞክራሲ ህልም በአጭር ተቀጭቷል::

አንደዚህም በመሆኑ የአራት ዓመቱ ፍሬ ቢስ ሂደት ሃገራችንን ምንም ርምጃ ወደፊት ስላላስኬዳት አሁንም አንደተላንቱ የሰላማዊ ዲሞክራሲያዊ ለውጥ በሮች ተጠርቀመው በመዘጋታቸው መጭው ጊዜ ለህዝቦቻችን የበጥበጥና የትርምስ ጊዜ አንዳይሆን አንሰጋለን:: አንድ ህብረተሰብ አንዳለ ለጭቆና አገዛዝ እጁን ይሰጣል ብለን ጨርሶ ስለማናምን የሽግግሩ ዘመን ተጠናቀቀ የሚባለው ለሃገራችን ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ባመጣ በመሆኑ ትግሉ የጠየቀውን መስዋእትነት እየጠየቀም ቢሆን ይቀጥላል::ለተገዢዎች ችግር ዘላቂ መፍትሄም አስኪሰሰጠ ድረስ በህዝባችን ላይ በግድ የተጫነው ሰነድ ለገዢዎችም ይዘታ ዘላቂነት አንደማያተርፍ ግልጽ ነው:: በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመን ለአጼ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ተመቻቸቶና "ዘውዱ ለዘለዓለም ከአጼ ኃይለሥላሴ ዘር ሳይወጣ ይኖራል" ብሎ ይደነግግ የነበረው ህገመንግሥት ከሳቸው አድሜ አላለፈም::በደርግ ዘመን ለደርግ አገዛዝ ተዘጋጅቶ "የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ተጠናቀ አስከሶሻሊዝም ግንባታ ድረስ" ሳለው ረዥም የታሪክ ዘመን የሃገሪቱ መመሪያ ሰነድ ተብሎ የነበረው ህገመንግሥት ከደርግ ያለፈ ዘላቂነት አልነበረውም:: ዛሬም ቢሆን በኢህአዴግ ለኢህአዴግ ተሰናድቶ በአቶ መለስ ዜናዊ አነጋገር "ከዚህም ትውልድ አልፎ ለሚቀጥለውም" ያገለግላል ተብሎ የተተነበየለት ህገ መንግሥት ከኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት ዘለቆ አንደማይሄድ ለአንዲት ደቂቃ አንኳን አንጠራጠርም::

የኢትዮጵያ ዲሞክራቶች ጭንቀት የትግሉ መቀጠል ወይም አለመቀጠል ጥያቄ አይደለም:: ትግሉ መቀጠል አለበት:: ይቀጥላል:: ችግሩ ይህ ሳይሆን መጭው የትግል ዘመን ገዢዎቻችንና የሃገራችን ጠላቶች አንደሚመኙት የትርምስና የውዥንብር፣ የእልቂትና የደም መፋሰስ እንዳይሆን ታጋይ ኃይሎች ጥራት ባለው የጋራ ዓላማ ተሳስረው በአንድነት በመታገል ሃገሪቱንና ህዝቦቿን ከተደገሰላቸው ጥፋት እንዴት ያድኑ ለሚለው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የመስጠት ችግር ነው::

ለዚህ ሃገርን ከጥፋትና ከትርምስ የማዳን ታሪካዊ ተልእኮ ብቁ ለመሆን ከፈለግን ከወዲሁ ለትግል ስንነሳ ስለመጭው የትግል ዘመን ራሳችንን በምንም ዓይነት ማታለል አንችልም:: የአስቸጋሪ፣ የተሰበጣጠረና የውስብስብ ትግል ዘመን ከፊታችን ይጠብቀናል::

ይህ የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚጠይቀው ከባድ ነገር በመሆኑ አይደለም:: የገዢዎች አብሪትና ይህንን አብሪት የሚያገዝ የባእድ ኃያላን እውርና አርቆ አስተዋይነት ያነሰው ወገናዊነት ተጋረጠበት አንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ የማይመስል ነገር አይጠይቅም:: ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ በታወቀት መስፈርቶች መሠረት ነጻና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ:: ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁትን መርሆዎች ያካተተ ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት:: ለዚህ ግልጽና ዲሞክራሲያዊ ዓላማ መሳካት የግድ መታገል፣ መስዋት አለብህ ተባለ አንጂ ይህ ሰማእት ህዝባችን ሌላው ቀርቶ ዛሬ ለድፍን አፍሪካ በመዳረስ ላይ ካለው የዲሞክራሲ ጸዋ ተጨማሪ የሚጠይቀው ምንም ነገር የለውም:: በበኩላችን ኢህአዴግ ተስማማ አልተስማማ፣ ባእዳን ኃያላን ይህ የኢትዮጵያ ህ

ዝብ ሀሰም ገባቸው አስገባቸው፣ ኢትዮጵያ ከዚህ ዱፍን ዓለምን ከማዳረስ ላይ ካለው የበጎ ለውጥ አውሎንፋስ ተነጥላ የምትቀርበት ምንም "የተለየ እርግማን" አለባት ብለን ስለማናምን ህዝባችን ለነዚህ ዓላማዎች በአዲስ መንፈስ ተነሳስቶ እንዲታገል ከመቀስቀስ ሌላ ምንም ምርጫ የለንም::

መጭው ዘመን የአስቸጋሪ ትግል ዘመን ይሆናል:: ዲሞክራሲ በሌለበትና ገዢዎች ለራሳቸው ካዘጋጁት ምርጫ ይበልጥ ዲሞክራሲ ይፈልቃል ብለን ራሳችንን አናታልልም:: ከህገ መንግሥቱ በፊት በተጨባጭ ሲረገጡ የነበሩ መብቶች ምንም ዋስትና በሌለው ሁኔታ በወረቀት ላይ ስለሰፈሩ ብቻ ይረጋገጡልናል የሚል እምነት የለንም:: በተጨባጭ ባለውና በሚለፈፈው መሃከል ያለው ክፍተት እየሰፋ እንጂ እየጠበበ የሚሄድበት ሁኔታ አይኖርም:: በዚህም ልክ ገዢዎች ይበልጥ እየተጋለጡና የሚይዙትና የሚለቁት እየጠፋቸው ተናካሽነታቸው እየጨመረ የህዝቡም ተቃውሞ በአስከፊ ሁኔታ ውስጥ እየሰፋና እየተጠናከረ ለመሄድ ይገደዳል:: ጭቆናና ተቃውሞ ተያይዘው ያድጋሉ::

የትግሉ አስቸጋሪነት በኢህአዴግ ጸረ ዲሞክራሲያዊ ድርጊቶች እየተበራከቱ መሄድ ብቻ የሚገለጽ አይደለም:: በጋራ ትግላችን አይለን ራሳችን በሃገራችን ያለውን ሚዛን ለዲሞክራሲያዊ ኃይሎች እንዲያደላ እስክናደርገው ድረስ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትግላችን ብቸኝነት የሚያጠቃው ትግል እንደሚሆን እንጠብቃለን:: ባእዳን ኃያላን መንግሥታት ምንም እንኳን ይህንን ህዝባችንን ለፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ፣ ሃገራችንን ለትርምስ የሚዳርግ ህገ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ ብለው በማሞካሸታቸው ሊከተል ለሚችለው ችግር የማይናቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ ቢሆንም ይበልጥ ጠንካሮች ካልሆንን ይበልጥ ዲሞክራሲያዊ ናችሁ ብለው አይደርሱልንም:: እርግጥ አልፎ አልፎ ኢህአዴግ ሲያበዛውና ለወዳጅም አስፈሪ እየሆነ ሲሄድ ርባናም ሆነ ክትትል የሌላቸው ውግዘቶችና መግለጫዎች ይኖራሉ:: ነገር ግን የሆነ ጥቅም እስካላየ ድረስ ለኢትዮጵያ ሰላምና ዲሞክራሲ ከና እኩል ተቆርቋሪው ጽኑ ዲሞክራሲያዊ አቋም ይኖራቸዋል ካለን ካለፉት ዘመናት የሃገራችን ታሪክም ሆነ ሌላው ቀርቶ በቅርቡ በሩዋንዳ የሚለፉን ደም ከደረቀ በኋላ ሲደርሱ ካየነው ክስተት ምንም ትምህርት አልቀሰምንም ማለት ነው::

በውስጥም በውጭም አስቸጋሪ የትግል ዘመን ስላለን ተስፋ እንቁረጥ ማለታችን እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ታጋይ ኃይሎች ለዲሞክራሲና ብሄራዊ ዓላማችን ለመክፈል ለምንገደደው መስዋእትነት ራሳችንን በይበልጥ እናዘጋጅ፣ የትግል አንድነትና ትግግዛችንን እናዳብር፣ ማንም ሆነ ማንም የጭቆናና የእብሪታዊ ርምጃዎች ሰለባ ሲሆን በተቻለን አብረን እንቁም ማለት ነው:: ብቸኝነታችንንም የጠቀምነው ተስፋ እንድንቆርጥ አይደለም:: በዲፕሎማሲውም መስክ የምናካሂደውን ትግል ርግፍ አርገን እንተወው ለማለት አይደለም:: ቢያስስ ቢያንስ ሃገራችን ችግር ላይ ስትወድቅ ብቸኝነትም አብሮ የሚያጠቃት መሆኑን ከፋሽስት ጣልያን ወረራ ጀምሮ በተደጋጋሚ ያየነው ተጨባጭ ሃቅ መሆኑን ተገንዝበን በማንም ሆነ ማንም ላይ ሳንተማመን በህዝባችን ላይ እንመካ፣ ህዝባችንንም በዚሁ መንፈስ እንምራው፣ ትግላችን አጀንዳ ውስጥ የብሄራዊ ነጻነታችንና ክብራችንም ጉዳይ ተገቢ ቦታውን ይያዝ ማለት ብቻ ነው::

ትግሉ ስብጥርጥር ይሆናል ለዚህም እንዘጋጅ ብለናል:: የትግል ስልት ምርጫ የሌላቸው፣ ለህልውናቸው ከባእዳን ድጋፍና ከአመጽ ሌላ [illegible] የማይሆንላቸው አናሳ የሆኑ ጸረ ህዝቦች ብቻ ናቸው:: ባለፉት አራት ዓመታት እንኳን እንዳየነው የህዝቦች የተቃውሞ ትግል ከአሸዋ የበዙ ገጽታዎች ይኖሩታል:: እና ፈቀድነውም አልፈቀድነው፣ ተመኘነውም ጠላነው የተለያዩ የትግል ስልት የሚከተሉ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ይኖራሉ:: ህገ መንግሥቱን ተቀብለው እሱ ደነገገ የተባለውን መብት እንቀጽ በስ

ንቀጽ እየጠቀሱ የኢህአዴግን መንግሥት በገዛ ህጉ ለመፋለም የሚመርጡ ኃይሎች ይኖራሉ:: ህገ መንግሥቱን በይዘቱም ሆነ በአጸዳደቁ ሂደት ተቃውመው በዲሞክራሲያዊ ሂደት ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት ብለው በሰላማዊና ህጋዊ ዘዴ ኢህአዴግን የሚፋለሙ ኃይሎች ይኖራሉ ለዚሁ ዓላማ ሰላማዊና ህቡእ የትግል ስልት መርጠው በዚያም በኩል ሊሰማሩ የሚመርጡ ወይም የሚገደዱ ዲሞክራት ዜጎች ይኖራሉ:: በመጨረሻም እና ፈቀድነው አልፈቀድነው ለዚሁ ዓላማ ኢህአዴግን በመጣበትና ሊጸና በሚፈልግበት የአመጽ ሂደት በጦር ሜዳ ለመፋለም የሚገደዱ ኃይሎች ይኖራሉ:: የትግል ስልት ምርጫ የማይኖረው ጸረ ህዝቡ ኃይል ብቻ ነው::

ስስተና ከፍ ብለን የጠቀስናቸው አስቸጋሪነትና ስብጥርጥርነት መጭውን ትግል ውስብስብ ያደርጉታል:: የኢህአዴግ ጭቆናና ዓለም አቀፍ ብቸኝነታችን ራሳቸው የክፍፍልና የውዝግብ ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ:: በተሰበጣጠሩ የትግል ስልቶችም ሆኑ ታክቲኮች መሰማራት አንዳንድ ታጋዮችን የጋራ የሆነ የዘላቂ ሰላምና የአስተማማኝ ዲሞክራሲ ዓላማ እንዳለ ሊያስረሳቸው ይችላል:: የጋራ ዓላማ እንዳለ መሳትን የመሰለ ለክፍፍል ንጣፍ ሊሆን የሚችል ነገር እንደሌለ በገዛ የትግል ታሪካችን በተደጋጋሚ ያየነው ነው:: በዚህ ላይ ኢህአዴግ በእርግጥም ከጦር የሚፈራውን የሰላማዊና ፖለቲካዊ የህዝብ ትግል ለመከፋፈልና ቅስሙን ለመስበር ሰርጎ ገቦችን በሠፈራችን ይለቅብናል:: በራሱ በዲሞክራሲው ሠፈር ዛሬ ዋናው ጥያቄ የትግል አንድነት ሳይሆን የነሱ ማበጥና የበላይነት ጥያቄ የሚመስላቸው፣ ኃይሎች ኢህአዴግን በቀጡ ለመዋጋት በሌሎች ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አስከሬን ላይ ማለፍ ያለባቸው የሚመስላቸው ኃይሎችም ይኖራሉ:: በዚህ ሁሉ ላይ ባእዳን ኃያላን ለኢህአዴግ አናሳና ጸረ ህዝብ አገዛዝ የማቴርያል፣ የፋይናንስ፣ የጦር፣ የዲኘሎማሲና የፖለቲካ ድጋፍ ከመለገስ አልፈው አያገባቸው በመግባት በዲሞክራሲያዊው ሰፈር ገብተው አንዱን እያነሱ ሌላውን እየጣሉ ሊፈተፍቱና ሊከፋፍሉ የሚሞክሩበት ወጥመድ ይኖራል::

እነዚህን ሁሉ ከወዲሁ ነቅተን ካልተገነዘብናቸውና የኢትዮጵያም ህዝቦች ነቅተው እንዲዋጉአቸው ካልቀሰቀስን ውጤቱ አደገኛ ውዥንብር ይሆናል:: እንዲህ ዓይነቱ ውዥንብር ደግሞ ለአዲስ የመከራና የትርምስ ዙር በር ከፋች እንደሆነ በሱማሊያ ያለው ሁኔታ ህያውና አሳዛኝ ማስተንቀቂያ ነው::

የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች የመጭው ትግል አስቸጋሪነት ተስፋ ሳያስቆርጣቸው ስብጥርጥርነቱ ሳይከፋፍላቸው፣ ውስብስብነቱ ግራ ሳያጋባቸው ታሪክ ለጣለባቸው ከባድ አደራ ብቁ ለመሆን እጅግ መጣር ይኖርባቸዋል:: በተለይ ዛሬ የአንድ አናሳ ጸረ ህዝብ የርእዮተዓለም ምርጫና ድርጅታዊ ኘሮግራም የአንድ ሃገር የበላይ ህግ ተብሎ የሸገገረ ዘመን ተገባደደ እየተባለና ኢህአዴግ በባእድ ኃያላን ታጅቦ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዙን ለመዘርጋት በተዘጋጀበት ወቅት ለዚህ ብቃት ስለትግል አንድነት ማውራት ብቻ አይበቃም:: ለዚህ መሠረት የሚሆን የዓላማ ጥራትና አንድነት እንደህይዎት እስትንፋስ የሚያስፈልግበት ወቅት ነው::

ከዚህ ተጨባጭ ሁኔታና እና የኢትዮጵያ ታጋይ ኃይሎች በትከሻችን ላይ ወድቋል ብለን ከምናምነውና ከምንቀበለው ታሪካዊና ብሄራዊ ሃላፊነት በመነሳት፣

<u>አንደኛ</u> ህብረተሰባችን ከፈላጭ ቆራጭ ጸአናሳ ኃይሎች አገዛዝ በጠቀላላው ህዝብ ፈቃድ ወደተገነባ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ ማለቂያ ከሌለው የጦርነትና የግጭት ባህል ወደ ዘላቂ ሰላም የሚሸጋገረው በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ነጻና ርእታዊ ምርጫ ሲካሄድና በዚህም አማካኝነት አሁንም በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝቦች በሙሉ የኔ ብለው የሚያምኑት፣ የሚያከብሩትና የሚንከባከቡት ህገ መንግሥት ላይ ተስማምተው የህግ የበላይነት እውን የሆነበት ሥርዓት ስንመሰርት ብቻ በመሆኑ

<u>ሁለተኛ</u> ይህ ግልጽ ዓላማችን ፈላጭ ቆራጭነትን ታግለን የኢትዮጵያ ህዝቦች እዲላ

ቸውን በራሳቸው የሚወስኑበት ዲሞክራሲያዊ ቅድመ ሁኔታ ለማመቻቸት እስከሆነ ድረስ ከድል ባሻገር ሊኖሩ በሚችሉና ሁኔታዎች ዮርአፀተዓለም፣ የፖለቲካ አመለካከትም ሆነ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፖሊሲ ወደፊት ለህዝብ ምርጫና ዳኝነት ሊተው በሚገባቸው ሳቢያ የትግሉን ዓላማ አንድነት ጥራት ማደፍረስና የትግል አንድነትን ቀስም መስበር የሰላምና ዲሞክራሲ ጠላቶችን በቀጥታ ማገዝ መሆኑን በማመን፣

<u>ሶስተኛ</u> የትግል ዓላማችን ነጻና ርእታዊ ምርጫ ብሎም ዲሞክራሲያዊ ህገመንግስት እስከሆነ ድረስ በዚህ ዘላቂ ዓላማ ክልል ውስጥ የተለያዩ ኃይሎች ካሉበት ተጨባጭ ሁኔታ እየተነሱ የሚቀይሷቸው የተለያዩ የትግል ታክቲኮች፣ ስትራቴጂያቸና የሚወስዷቸው አቋሞች የከፋፋለና የንትርክ ምንጭ ሆነው የትግል ዓላማ አንድነታችንን ቀስም መስበርና ህዝቡንም ግራ ማጋባት እንደማይገባቸው በማመን፣

<u>አራተኛ</u> ገና ለረዥም ጊዜ የኢትዮጵያ ታጋዮች ለንሰዋለትና ለንታገለለት በመገደድ ላይ ያለነው የነጻ ምርጫና የዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት ቅዱስ ዓላማ ይዘትና ትርጉም ምን እንደሆነ ግልጽ ቢሆንም ቃሉ በተጨባጭ ምን ማለታችን እንደሆነ ለኢትዮጵያ ህዝቦችም፣ በየድረጅቶች ለተካተቱ ታጋዮችም፣ ለሃገራችን በጐ ለሚመኙ የዓለምአቀፉ ኮሙኒቲ አባላትም በይፋና በዝርዝር ማስታወቅ ይህንን ትግላችንን ያግዛል ብለን ስላመንን

እና ስማችን ከዚህ በታች የተዘረዘረው ድርጅቶች በኢትዮጵያ ጦርነትም ሆነ የጦርነት አደጋ በማያጓግም ሁኔታ እንዲወገዱ፣ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን፣ ኢትዮጵያውያን በእኩልነትና በወንድማማችነት መንፈስ አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ፣ የብሔርና የብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የተረጋገጠባት፣ የሰው ልጅ መብቶች ሙሉ በሙሉ የተከበረባት፣ የህግ የበላይነት እውን የሆነባትና በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የምትተዳደር አገር ለመመሥረት በር ከፋችና ቅድመ ሁኔታ ለሆኑት ለነጻ ምርጫና ለዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት በጋራና በመተጋገዝ መንፈስ ለመታገል ስንነሳ ዝርዝር ዓላማችንን እንደሚከተለው እነሆ እናቀርባለን::

<u>ነጻ፣ ርእታዊና ሃቀኛ ምርጫ</u>

ነጻ፣ ርእታዊና ሃቀኛ ምርጫ ስንጠይቅ ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካገኙትና የኢህአዴግ የምርጫ ሂደቶች ከሚረገጧቸው መርሆዎች አልፈን የምንጠይቀው ምንም ነገር የለም:: የኢህአዴግ የምርጫ ሂደቶች ከነዚህን መርሆዎች አንዳንዶቹን በይፋ በመጻረር፣ ሌሎችን ደግሞ ከአንገት በላይ ከተቀበሉ በኋላ በተግባር በመሻር የተካሄዱና የሚካሄዱ የሸፍጥ ሂደቶች ናቸው::

የችግሮቹ ሁሉ ምንጭ በምርጫዎች ይወዳደራሉ ከሚባሉት ኃይሎች መሃከል አንዱ ብቻውን የሃገሪቱን የጦርና የፖሊስ ኃይል፣ የመንግሥት መዋቅር፣ የሚገናኛ ብዙሃን ተቋሞች፣ የመንግሥትንና የፋይናንስና ቀሳቀስ ኃይል፣ የመንግሥትን ዲፕሎማሲያዊ ቅባሉት ለጠባብ ወገናዊ ዓላማው ስለተጠቀመባቸው ብቻ አይደለም:: ይህ ድርጅት ይህ ሁሉ አላንስ ብሉት የምርጫውንም ሂደት ከዳር እስከዳር ብቻውን በመቆጣጠር ምርጫዎች ሁሉ በአዘገጓጀታቸውና በአካሄዳቸው አጅግ ተጠመው በውጤታቸውም በሃቅ በሃገሪቱ ያለውን የሃይል አሰላለፍም ሆነ የህዝቦቿን ፍላጎት እንዳያንጸባርቁ አርጓቸዋል::

ከዚህ በመነሳት የሃገራችን ችግሮች በህዝብ ፈቃድ፣ በነጻ፣ ርእታዊና ሃቀኛ ምርጫ ይፈቱ ስንል አንደኛ ከታወቀት ዓለም አቀፍ የምርጫ መርህ ውስጥ ኢህአዴግ በይፋ የሚሸራቸው ይከበሩ፣ ሁለተኛ ደግሞ ከአንገት በላይ እየተቀበለ በተጨባጭ የሚሸ

ራቸው መርሆዎች በተግባር ይረጋገጡ በማለት ልናቆም አንችልም:: ከዚሁ ጋር አያይዘን በሃገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የምርጫዎች ዝግጅት ከገዥዎች መዳፍና ቁጥጥር ሥር መውጣት አለበት ብለን እናምናለን::

ስለሆነም በሃገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ነጻ፣ ርእታዊና ሃቀኛ ምርጫ ተካሄደ ችግሮቻችንን በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ዘዴ ለመፍታት የሚያስችለን የምርጫ ሂደት ፈር ለማስያዝ ለሚከተሉት ዓላማዎች ትግሉን እንቀጥላለን፣

## 1ኛ/ የዲሞክራሲያዊ ሂደትና የምርጫ ኣገባብ ማቋቋም

የእስከዛሬውም ሆነ የዛሬው ውድቀትና ምርጫዎችን ሁሉ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ፍሬ ቢስ ያደረጋቸው ምርጫዎቹንና እነዚህ ሂደቶች ዲሞክራሲ ባልተከበረበትና የሰው ልጅ መብቶች በተረገጡበት አካባቢ፣ በገዥዎች ተዘጋጅተው በነሱ ቁጥጥር መካሄዳቸው ነው:: ዲሞክራሲና የሰው ልጅ መብቶች በማንኛውም ወቅት አስፈላጊ ቢሆኑም በምርጫ ወቅት ደግሞ በተባበሩት መንግሥታት መሰፈርቶች መሠረት ለነጻና ርእታዊ ምርጫ "ቅድመ ሁኔታ መብቶች" /ፕሬሪኩዊዚት ራይትስ/ ተብለው የተጠቀሱት ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እስከተባለ ድረስ የምርጫውን ሂደት፣ አስተዳደር፣ ቁጥጥር...ከተወዳዳሪዎቹ ለአንዱ ብቻ መተው በየትም የሌለ አሠራር ነው::

በመሆኑም እንደና በምርጫው አኳያ ቅድመ ሁኔታ መብቶች የሚባሉት እንዲከበሩና በሃገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ እንዲመቻች፣ ሁለተኛ ደግሞ ዘቀ ብለን የምንዘረዝራቸው የነጻ፣ ርእታዊና ሃቀኛ ምርጫ በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን የሚከታተል ወይ ከዋና ዋና ተወዳዳሪዎች የተውጣጣ፣ ወይ እነሱ የተስማሙበትና ከነሱ ውጭ የተቋቋመ ገለልተኛና በጋራ ስምምነት የተሰየሙ የውጭ ታዛቢዎች ያሉበት አንድ የዲሞክራሲያዊ ሂደትና የምርጫ ኣገባብ መቋቋም ይኖርበታል::

## 2ኛ/ አንድ ምርጫ ነጻ ምርጫ እንዲባል

የዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብት አዋጅ አንቀጽ 21/1/ ማንም ዜጋ በሃገሩ መንግሥት አሠራር በቀጥታም ሆነ በነጻ በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት የመሳተፍ መብት አለው ብሎ ሲደነግግ ነጻ ለሚለው ቃል በተለይ በዛሬይቱ ዓለም አጠቃላይ ስምምነት አለ:: የአንድ ምርጫ ነጻ መሆን የሚለካው የህዝቡን የፖለቲካ ፍላጎት በትክክል ለማንጸባረቅ በሚችልበት ሁኔታ ተዘጋጅቷል ወይም አልተዘጋጀም ለሚለው ጥያቄ እንደሚገኘው መልስ ነው:: በትክክል የህዝቡን የፖለቲካ ፍላጎት እንዲያንጸባርቅና በዓለም አቀፍ መርሆዎች መሠረት ነጻ እንዲባል አንድ ምርጫ፣

ሀ/ በዲሞክራሲያዊ አካባቢ፣ የሰው ልጅ መብቶች በተከበሩበትና ከመንግሥታዊ ኃይሎችም ሆነ ከሌሎች አካባቢ ምንም ዓይነት ዛቻና ማስፈራራት በማይታይበት ሁኔታ መካሄድ አለበት፣

ለ/ በዓለም አቀፍ የሰው ልጅ መብት አዋጅና በሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የተረጋገጡት በተለይም ደግሞ ምርጫን በተመለከተ "ቅድመ ሁኔታ መብቶች" የተባሉት የሃሳብ፣ የመጻፍ፣ የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀትና አድልዎ የሌለበት ዳኝነት የማግኘት መብቶች መከበር አለባቸው

ሐ/ ዛቻና ማስፈራራትን ፍሬ ቢስ ለማድረግ የምርጫውን ምስጢርነት ከማወቅ አልፍ መራጩ ህዝብ በዚህ ምስጢራዊነት አመኔታ እንዲኖረው በቅድሚያ ሰፊና ገለልተኛ የሆነ የሲቪክ ትምህርት ዘመቻ መካሄድ ይኖርበታል::

እነዚህ ጥያቄዎችና መሰፈርቶች ቀለልና ግልጽ በመሰሉም ትላንትም ሆነ ዛሬ በሃገራችን የምርጫ ታሪክ ተሟልተው አያውቁም። ዛሬ በተቃዋሚ ኃይሎች ላይ ያለው የአፈና፣ የግድያ፣ የእስራት፣ ያለፍርድ መያዝና ከህግ ውጭ መንገላታት በሰፊው ይካሄዳል። ለአንድ ነጻ ምርጫ ቅድመ ሁኔታ መብቶች የተባሉት ሁሉ አንዳንዴ እነዚህን መብቶች በመፍቀድ ስም ወጥተው በሚያፍኑቸው የኢህአዴግ ህጎች፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በዚሁ ድርጅት የዘፈቀደና ህገወጥ ርምጃዎች ተረግጠዋል። ይህ ሁሉ ግፍና ህገወጥ ድርጊት እንዲታረም ሲባል አቤት የሚባልበት ከኢህአዴግ ቁጥጥር ውጭ የሚሠራ የዳኝነት ነጻነት ያለው ገለልተኛ የለም። አንዳንድ ዳኞች ከመመሪያ ውጭ የመንግሥትን ጥቅም የሚጻረር ፍርድ ሲሰጡ ይህ ብያኔያቸው በመንግሥት ላይ አይጸናም። ባጭሩ ይህ ሁሉ ከተቃዋሚ ኃይሎችም አልፍ በህዝቡ ላይ በሚያባድረው ስሜት የተነሳ ዛሬ ባለው ሁኔታ በሃገሪቱ ከዛቻና ማስፈራራት ነጻ የሆነ ምርጫ ለማካሄድ አይቻልም።

በመሆኑም ከፍ ብለን የጠየቅነው የዲሞክራሲያዊ ሂደትና የምርጫ ኣገባብ አንዱና ዋናው ተግባሩ እነዚህ የነጻ ምርጫ ጸር ክስተቶች የሚወገዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ መሠረታዊ የመደራጀትና የፕሬስ ነጻነትን የሚያፍኑትን የኢህአዴግ ህግጋት ከጸረዲሞክራሲ ይዘታቸው እንዲጸዱ ማድረግ፣ የህግ በላይነት እንዳይጠስ የሚያስችሉ ዘዴዎችን መቀየስ፣ በአጠቃላይ የነጻ ምርጫ መሰፈርቶች ከሥራ ላይ የሚውሉበትን ዘዴ መሻትና ከሥራም ላይ መዋላቸውን መቆጣጠር ይሆናል።

35/ <u>አንድ ምርጫ ርትዓዊ እንዲባል</u>

ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ አንቀጽ 21/3/ አንድ ምርጫ ርትዓዊ እንዲሆን የዜጎችን የእኩልነትና የአጠቃላይ ተሳትፎ መብት ማረጋገጥ እንዳለበት ሲደነግግ በአንቀጽ 2 ደግሞ ለዚሁ ተሳትፎ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በቀለም፣ በፖለቲካና ሌላ አስተሳሰብ፣ በብሄራዊ ማንነትና በማህበራዊ ማእረግ በመሳሰሉ መሰፈርቶች ሳቢያ በዜጎች ላይ አድልዎ እንዳይደረግ ይከለክላል። እነዚህን መሰፈርቶች ያላከበረ ምርጫም ርትዓዊ ሊባል አይቻልም። በመሆኑም ርትዓዊ ምርጫ ስንል የምንጠይቃቸውና የኢህአዴግ የምርጫ ህግ የረገጣቸው መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው

ሀ/ የዜጎች እኩል፣ አጠቃላይና አድልዎ የሌለበት ተሳትፎ። ይህ ማለት አንድ ምርጫ ርትዓዊ እንዲባል በያለበት ከሚሰራባቸው የአድሜ፣ የዜግነትና የአእምሮ መታወክ የተሳትፎ ማገጃ አነስተኛ መሰፈርቶች በተጨማሪ ቋንቋን፣ የፖለቲካ አቋምን፣ የተንዛዛ የነዋሪነት ዘመን መሰፈርትን ተመርኩዞ ተሳትፎን የሚያግድ የምርጫ ህግ መኖር የለበትም ማለት ነው።

ለ/ <u>አንድ ዜጋ አንድ ድምጽ</u> ይህ ማለት ከፍ ብለን በጠቀስናቸው አነስተኛ መሰፈርቶች ምክንያት ከተሳትፎ ያልታገዱ ሁሉ ድምጽ ይኖራቸዋል ማለት ብቻ አይደለም። የእያንዳንዱ መራጭ ዜጋ ድምጽ እኩል ክብደት የሚያገኝበት ዘዴ ካልተቀየሰ የአንድ ምርጫ ርትዓዊነት ሊረጋገጥ አይቻልም ማለት ነው።

ሐ/ ህጋዊና የአስተዳደር ዋስትናዎች። ይህ ማለት የምርጫው አዘገጃጀትና አስተዳደር በሁሉም ዘንድ ገለልተኝነታቸው አጠያያቂ ባልሆኑ ተቋሞች መካሄድ ይኖርበታል ማለት ነው። ከዚህም ተያይዞ በስልጣን መባለግ የተከለከሉና የምርጫውን ሂደት ሊበክሉ የሚችሉትን ተግባራት ሁሉ ህገወጥ ማድረግና መቅጣት፣ ለመራጩ ህዝብ አመኔታን በሚሰጥ ሁኔታ ገለልተኛ ታዛቢዎችን ማሰማራት፣ ድርጅቶችና ሌሎች ተወዳዳሪዎች በመገናኛ ዘዴዎች የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ማመቻቸትን ይጠይቃል።

የኢህአዴግ የምርጫ ህግጋትና አሠራር፣ በዚህም መሠረት የሚካሄዱት ምርጫዎች

 

እነዚህን የርእታዊ ምርጫ ዓለምአቀፋዊ መስፈርቶች በይፋ የሚረግጡ ናቸው::

እሩስ፣ አጠቃላይና አድልዎ የሌለበት ተሳትፍ የሚለውን የርእታዊ ምርጫ መስፈርት በመርገጥ ዜጎችን በቋንቋ፣ በፖለቲካ አቋም በተንዛዛ የነዋሪነት ዘመን ቅድመሁኔታ መስፈርት ሰበብ ከምርጫው ሂደት ሙሉ ተሳትፍ እንዳይኖራቸው አግዷል:: በዚህም በሃገር ውስጥ አንዳንድ ክፍሎች፣ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ደግሞ እንዳሉ በሙሉ የተገለሉበት ምርጫ በመሆኑ የኢህአዴግ አሠራር በምንም ዓይነት ርእታዊ ሊባል አይችልም::

አንድ ዜጋ አንድ ድምጽ የሚለውን መሠረታዊ የርእታዊ ምርጫ መርህ በመሻር የመረጠው የምርጫ ሥርዓት ተሳትፍ ከተፈቀደላቸው ዜጎች መሃከል እንኳን የኢህአዴግ ደጋፊዎች ድምጽ ብቻ ከቁጥር የሚገባበት፣ የተቃዋሚዎች ድምጽ በየምርጫ ክልሉ ባክኖ የሚቀርበት ሥርአት በመሆኑ የነዚህኖቹን ዜጎች ድምጽ እኩልነት የነሳ አሠራር ነው:: በአንድ ዞር አብላጭ ድምጽ በሚለው መርህ ላይ የተመሠረተው የኢህአዴግ የምርጫ ሥርአት ምንም እንኳን በሁለት ዋና ዋና ነባር ፓርቲዎች ሥርዓት ለሚተዳደሩ ነባር ዲሞክራሲዎች የሚሠራበት ቢሆንም እንደኢትዮጵያ ላሉ በሽግግር ላይ ለሚገኙና በህዝብ ተሳትፍ ህገመንግሥት ለማጽደቅ ለሚሞክሩ ህብረተሰቦች እንደማይሰራ በምርጫ ስም የአንድ ድርጅት የፖለቲካ ፕሮግራም የአንድ አገር የበላይ ህግ ተብሎ ሲጸድቅ ማየት መብቃታችን ህያው ማስረጃ ነው::

ህጋዊና የአስተዳደር ዋስትናዎች የተባሉትን መስፈርቶች በይፋ በመሻር በመንግሥት ስም የተቆጣጠረው አንዱ ተወዳዳሪ ኃይል የምርጫውን ዝግጅትና ሂደት ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠርበት የራሱ የሆነ የምርጫ ኮሚሽን በማቋቋም፣ ይህንን መሠረታዊ የሆነ የርእታዊ ምርጫ ረግጧል::

ለመራጩ ህዝብም ሆነ ለተወዳዳሪ ድርጅቶች የዲሞክራሲያዊ ሂደት ዋስትና ሊሰጡ ይችሉ የነበረት ባአዳን ታዛቢዎች ባላቸው ወገናዊነት የተነሳ ነጻነት፣ ርእታዊነትና ሃቀኝነት የጎደላቸውን የኢህአዴግ ምርጫዎች ቢያወግዙም ሳምንታት ቆይተው ያወገዙትን ምርጫ ውጤት ሲቀበሉ/በመታየታቸው የህዝብን ተዝብት እንጂ አመኔታ ሊያገኙ አልቻሉም:: በዚህም የተነሳ ባአድ ኃያላን በሌሎች አካባቢዎች ለምርጫዎች ርእታዊነት ብዙ አስተዋጽኦ ቢያደርጉም በኢትዮጵያ ግን እዚህ ግባ የሚባል ሚና መጫወት አልቻሉም::

በመሆኑም በኢትዮጵያ ርእታዊ ምርጫ እንዲከናወን የዲሞክራሲያዊ ሂደትና የምርጫ ኣካሄድ ከላይ የጠቀስናቸውን ዓለምአቀፍ መስፈርቶች የሚያካትት የምርጫ ህግ ማውጣት፣ ህጋዊና አስተዳደራዊ ዋስትናዎች የሚረጋገጡበትን ተቋሞች መመስረት፣ ዓለምአቀፍ ታዛቢዎች ፍሬያማ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ዘዴና ሃሳብ በመሸት እነሱንም በተግባር ማዋል ይኖርበታል::

4ና/ <u>አንድ ምርጫ ሃቀኛ እንዲባል</u>

የዓለምአቀፍ የሰው ልጅ መብት አዋጅ አንቀጽ 21/3/ እና ሌሎችም የሲቪልና ፖለቲካ መብቶችን የሚደነግጉ ዓለምአቀፍ ስምምነቶች አንድ ምርጫ ፍሬያማ እንዲሆን "ሃቀኛ" መሆን እንዳለበት ይደነግጋሉ:: በዚህ መስፈርት መሠረት ከተወዳዳሪዎቹ አንዱ ኃይል ባለው አመቺ ሁኔታ አለአግባብ በመጠቀም፣ የምርጫውን ዝግጅትና ሂደት በማጣመም፣ በማጭበርበርና በሸፍጥ የምርጫውን ውጤት መበከል ከቻለ ሃቀኛ ምርጫ ተካሄደ ማለት አይቻልም:: የአንድ ምርጫ ሃቀኛነት መለኪያ በውጤቱ በሃገሪቱ ያለውን የፖለቲካ ኃይሎች አሰላለፍ በተከከለ ማንጸባረቁ ላይ ነው:: ስለሆነም አንድ ምርጫ ሃቀኛ እንዲባል አስፈላጊ የሆኑትና የኢህአዴግ የምርጫ ሂደት የሚረግጣቸው መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው::

ሀ/ <u>የተለያዩ አማራጮች መኖር</u> ይህም ማለት መጀመሪያውኑ ለመራጩ ህዝብ የተለያዩ የርእዮተ ዓለም አዘማሚያዎች፣ የተለያዩ የፖለቲካ አማራጮች፣ የተለያዩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች የሚያንጸባርቁ ቡድኖችም ሆኑ ተወዳዳሪዎች ያለአንዳች ገደብ መቅረብ መቻል አለባቸው ማለት ነው:: ይህም ማለት በአንድ በኩል የተቃውሞ መብት መከበር አለበት፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች በነጻ ለመንቀሳቀስ ያላቸው መብት መጠበቅ አለበት ማለት ነው:: በሌላ በኩል በህዝብ ፊት እጩዎች የማቅረብ፣ አማራጮቻቸውን ያለአንዳች ገደብ የመግለጽ፣ ለዚህም ተግባር አድሎአዊነት የሌለበት የገንዘብና ማቴርያል ርዳታ የማግኘት መብታቸው መከበር አለበት ማለት ነው::

ለ/ <u>የተለያዩት አማራጮች ያለአድልዎ ለመራጩ ህዝብ የሚደርሱበትን ዘዴ መሸት</u> ይህም ማለት እነዚህ አማራጮች በመገናኛ ብዙሃንም ሆነ በሌሎች ዘዴዎች ለመራጩ ህዝብ እንዲብራሩለት፣ አንዱ ወገን ባለው አመቺ ቦታ በመጠቀም የራሱን እያሞገሰ የተቃዋሚዎቹን አማራጭ እያጥላላ ህዝቡ የሚያስፈልገውን ጥራት ማጣመም የለበትም ማለት ነው:: በተለይ መገናኛ ብዙሃን ከተወዳዳሪዎቹ በአንዱ ቁጥጥር ስር ብቻ በሚሠራበት ሁኔታ ይህ ጥያቄ ለተቃዋሚ ወገኖች ወረፋ በመስጠት ብቻ የሚሸን ጥያቄ አይደለም:: ተቃዋሚ ወገኖች በቀን አንድም ሁለትም ሰዓት ወረፋ ተሰጥቷቸው አቋማቸውን ለህዝብ እያብራሩ በቀረው ጊዜ በሙሉ መገናኛ ብዙሃን የተወዳዳሪውን መንግሥታዊ ድርጅት ሥራ፣ አስተሳሰብ አቋም አስመልክተው ፕሮፖጋንዳ ከተነዛባቸው አማራጮች ሁሉ በእኩልነት ቀረቡ ማለት አይቻልም:: በመሆኑም አንድ ምርጫ ሃቀና እንዲባል መገናኛ ብዙሃን ገለልተኛ የሚሆኑበት ዘዴ መፈለግ አለበት ማለት ነው::

ጠ/ <u>የመንግሥት መዋቅሮች ገለልተኛነት</u> ከተወዳዳሪዎቹ ድርጅቶች አንዱ በመንግሥትነት ስም ተቆምጠ የአንዱን አገር የፋይናንስም ሆነ የማቴርያል አቅም፣ የአስተዳደር መዋቅር፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ የጦር፣ የፖሊስና የጸጥታ ኃይሎችን ለወገናዊ ዓላማው ማራመጃ አርጉ ከተጠቀመባቸው የተለያዩ አማራጮች መቅረብ ቢችሉ እንኳን የምርጫው ውጤት ሊጣመምና የህዝቡን እውነተኛ ፍላጐት ላያንጸባርቅ ይችላል:: በተለይ እዛው በዛው መንግሥትም ተወዳዳሪ ድርጅትም የሆነው ኃይል በዚህ አመቺ ሁኔታው በመጠቀም አንዳንድ ክፍሎችን በጥቅም ሆነ በሌላ ተስፋ በመደለል፣ ሌሎች ክፍሎችን ደግሞ ለማስፈራራት ከተጠቀመበት በዚህ ሁኔታ የተካሄደ ምርጫ ውጤት ሃቀኝነት ይጎላዋል::

መ/ <u>የሲቪክ ትምህርት ጥያቄ</u> ይህ ማለት በተለይ እንደኢትዮጵያ ባሉ ከዘመናት ጭቆና እየተላቀቀ ወደ ዲሞክራሲ ለመሸጋገር በሚጥሩ አገሮች ህዝቡ ስለምርጫው ምንነት ስለሂደቱና አዘገጃጀቱ የሚያስረዳው የትምህርት ዘመቻ አስፈላጊ ነው ማለት ነው:: ይህ የሲቪክ ትምህርት ዘመቻ ማንን እንደሚመርጥ ሳይሆን ምርጫ ለምን? የት? እንዴት? መቼ? በመሳሰሉት ጥያቄዎች ላይ ያተኩረ ገለልተኛ ዘመቻ መኖር ጨጨጨጨ ይኖርበታል ማለት ነው:: በተመሳሳይ ሁኔታ በተካሄዱ ምርጫዎች እንደታየው ከሆነ ህዝቡ በምርጫው ምስጢራዊነት ሙሉ እምነት እስከሌለው ድረስ የሚፈልገውን ሳይሆን የሚጠበቅበትን ለመሥራት ስለሚገደድ የዚህ የሲቪክ ትምህርት ዘመቻ እዚህ ጥያቄ ላይ ማተኮር እንዳለበት ግልጽ እየሆነ መጥቷል::

እነዚህ ከፍ ብለን የዘረዘርናቸው የሃቀና ምርጫ መሥፈርቶች በሃገራችን እስከ ዛሬ በተካሄዱት ምርጫዎች በአንደናቸውም ተሟልተው አያውቁም:: ሁሉም አማራጭ የሌላቸው ምርጫዎች ነበሩ:: የመድበለ ፓርቲን ሥርዓት በአፍ ደረጃ ለመቀበል ቢገደድም ቀሉ ኢህአዴግ የተቃዋሚ ኃይሎችን እንቅስቃሴ በመግታት፣ አባሎቻቸውን በማሰርና በማሳደድ፣ ለይስሙላ በህዝብ ፊት የሚገጥሙትን "ተቃዋሚዎች" እሱ ራሱ በቅድሚያ በመምረጥ የመርጫውን ሂደት አሳዛኝም አስቂኝም አርጓታል:: መገናኛ ብዙሃንን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር

በማድረግ፣ በመንግሥት የፋይናንስና ማቴርያል አቅም እንዳሻው በመጠቀም፣ በፖሊሱና በሰራዊቱ ላይ ባለው ብቸና ቀጥጥር እንዳሻው ተቃዋሚዎችን በማሰር፣ በመግደል፣ በማሰደድ፣ ህዝቡንም በማስፈራራት ወዘተ በፈጠረው አካባቢ ምንም ዓይነት ሃቀኛ የሆነ ምርጫ እንዳይካሄድ አድርጓል::

በመሆኑም በሃገራችን ሃቀኛ የሆነ ምርጫ እንዲካሄድ የዲሞክራሲያዊ ሂደትና የምርጫ አካል ብለን ከፍ ብለን የጠየቅነው የጋራ አካል የተቃዋሚ ድርጅቶች የመንቀሳቀስና ሃሳብን በህዝብ ፊት የማስፋፋት መብት፣ መገናኛ ብዙሃን በአንድ ገለልተኛ በሆነ አካል ቀጥጥር ሥር በመሥራት እነሱም ገለልተኛ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለመሻት፣ በአንድ ተወዳዳሪ ድርጅት ቀጥጥር ሥር ያለው የመንግሥት ፋይናንስና ማቴርያል አቅም ያለአግባብ እየተሰራበት ለዚያ ቡድን ወገናዊ የምርጫ ጥቅም እንዳይውል ለመቆጣጠር፣ የመንግሥት የጦርና የፖሊስ ሠራዊት በማንኛውም መልክ ቢሆን በወገናዊነት የምርጫውጪ ሂደት ላይ ተጽእኖ እንዳያሳድር ዘዴዎች የሚሻ አካል መሆን ይኖርበታል::

* * *

## ዲሞክራሲያዊ ህገመንግሥት

በዚህም ጥያቄ ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከታወቁትና የኢህአዴግ ህገ መንግሥት በገለጸ ከሚረጋገጣቸው መርሆዎች አልፈን የምንጠይቀው ምንም ነገር የለም:: የምንጠይቀውና የምንታገለው የሃገሪቱ ህገ መንግሥት የሚከተሉትን ዋና ዋና ዲሞክራሲያዊ መርሆዎች በሚያካትት ሁኔታ እንዲደነገግ ነው::

1ኛ/ መሠረታዊ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ይረጋገጡ

ማንኛውም ህገ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ እንዲባል በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ የተደነገጉትን መሠረታዊ መብቶች ለመከበራቸው ህገመንግሥታዊ ዋስትና በሚሰጥ ሁኔታ መሠረት አለበት:: የኢህአዴግ ህገ መንግሥት እንደአጼ ኃይለስላሴና እንደደርግ ህገመንግሥታት እነዚህን መሠረታዊ መብቶች ደነገገ እንጂ የሚረጋገጡበትን ዘዴ የሚደነግጉ አንቀጾች የለውም::

2ኛ/ የህገ መንግሥት የበላይነትና ህገመንግሥታዊ ቁጥጥር ይኑር

ማንኛውም ህገ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ እንዲባል በተጨባጭ የሃገሪቱ የበላይ ህግ ሆኖ የሚያገለግልበት ነጻ የሆነ የቁጥጥር ዘዴ እንዲበጅለት ያስፈልጋል::ይህም ማለት የማንኛውም የመንግሥት ዘርፍም ሆነ ባለሥልጣን ፖሊሲ፣ ውሳኔና ድርጊት ህገ መንግሥትን ሊጻረረው እንዳይችል ከዚህ የመንግሥት ዘርፍና ባለስልጣን ነጻ የሆነና የውሳኔ መብት ያለው ተቆጣጣሪ አካል መኖር አለበት ማለት ነው:: የኢህአዴግ ህገ መንግሥት እንደደርግ ህገ መንግሥት የህገመንግሥትን የበላይነት ቢያውጅም ለዚህ ቁልፍ ተግባር የተሰየመ ከፖለቲካ ቁጥጥር ነጻ የሆነና የውሳኔ ሥልጣን ያለው አካል የለውም::

3ኛ/ የሥልጣን ክፍፍል መርህ በሥራ ላይ ይዋል

ማንኛውም ህገ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ እንዲባል በህግ አውጭው፣ በሥራ አስፈጻሚውና በዳኝነት የሥልጣን ዘርፎች መሃከል ቁጥጥርንና ሚዛናዊ አሠራርን፣ ተጠያቂነትንና የህዝብ ውክልናን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ሥልጣኑን አደላድሎ ማከፋፈል አለበት:: የኢህአዴግ ህገ መንግሥት እንደደርግ ህገ መንግሥት ከሥልጣን ክፍፍል መርህ ይልቅ የመንግሥት ስልጣን አንድ ወጥነትን የሚከተል በመሆኑ የመንግሥትን ከፍተኛ ሥልጣን ለአንድ "ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን አካል" ጠቅልሎ በመስጠት ዲሞክራሲያዊውን የሥልጣን ክፍፍል መርህ ይሽራል

4ኛ/ የዳኝነት ነጻነት ይረጋገጥ

ማንኛውም ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት ለአንድ ህብረተሰብ የህግ የበላይነትን ሲደነግግ ለዚህ አስፈላጊ የሆነውን የዳኝነት ነጻነት ዋስትና ባለው ሁኔታ የሚያረጋግጥ ነጻ የሆነ አካልም አብሮ መደንገግ አለበት:: የዳኝነት ነጻነት ማለት የዳኞች ነጻነት ማለት ነው:: ይህም ማለት የዳኞችን አሰያየምና ከሥራ መነሳት፣ ዝውውር፣ እድገትና ዲሲፕሊን የሚቆጣጠርና የሚከታተል ከመንግሥት ነጻ የሆነና ህገመንግሥታዊ ሀልውና ያለው አካል መደንገግ ማለት ነው:: የኢህአዴግ ህገመንግሥት እንደደርግ ህገ መንግሥት የዳኝነት ነጻነትን መርህ ቢቀበልም ለዚህ ተግባር ሥልጣኑና የአባላቱ ማንነት፣ አሠራሩና የነጻነቱ ልክ ተዘርዝረው የተደነገጉበት ግልጽ ዝርዝር የለውም::

5ኛ/ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት በተጨባጭ በሥራ ላይ ይዋል

ማንኛውም ህገ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ እንዲባል በመድብለ ፓርቲ መርሆዎች ላይ መመሥረትና ይህንንም በተጨባጭ ማስቻል አለበት:: ይህም ማለት የተለያዩ ርእዮተዓለማት፣ የተለያዩ የፖለቲካ አቋሞች፣ የተለያዩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች የሚያራምዱ ፓርቲዎች በህዝብ ፊት እንዲወዳደሩ፣ አብላጫ ድምጽ ያገኙት ለተወሰነ ጊዜ የመንግሥት

ሥልጣን ይዞ ይህንን የህዝብ ድጋፍ ያገኘ ፕሮግራማቸውን ከሥራ ላይ የሚፈቅድ ሰነድ መሆን አለበት ማለት ነው:: የኢህአዴግ ህገመንግሥት እንደደረገ ህገ መንግሥት የአንድ አናሳ ድርጅት ርእዮተዓለምና የፖለቲካ አቋም፣ የአንድ ድርጅት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች የአገሪቱ የበላይ ህግ ተብለው የተደነገጉበት ሁለገብና ፕሮግራማዊ ሰነድ ነው:: ይህንን የኢህአዴግ ፕሮግራም የማይቀበሉ ድርጅቶች ምርጫ አሸንፈው የመንግሥት ሥልጣን ቢይዙም አብላጭ የህዝብ ድጋፍ ያገኙበትን ፖሊሲ ከሥራ ላይ ለማዋል በቀላሉ እንደማይሻሻል ሆነ የተቀላለፈውን ህገመንግሥት ለማሻሻል ይገደዳሉ::ይህም አስከልሆነ ድረስ በኢህአዴግ ህገ መንግሥት ክልል ውስጥ የተለያዩ ፓርቲዎች በሥልጣን የሚፈራረቁበት ሁኔታ የለም::

6ኛ/ የህገመንግሥት መደንገግና መሻሻል ሂደት ዲሞክራሲያዊ ይሁን

አንድ ህገ መንግሥት የአንድ ሃገር የበላይ ህግነት የሚሰጠውን ሥልጣን፣ ቀባሉትና ክብር እንዲጎናጸፍ ከወዲሁ የህብረተሰቡ የተለያዩ ክፍሎች በሙሉ ተደራድረውና ተስማምተው የሚያጸድቁት የጋራ ሰነድ መሆን አለበት::ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት መደመሪያውኑ በዲሞክራሲያዊ ዘዴና በህብረተሰቡ የተለያዩ ክፍሎች ስምምነት የጸደቀ ሰነድ ተብሎ ስለሚገመት እንዲሻሻልም እንደዚሁ የጋራ ስምምነት ያስፈልገዋል:: ማለትም በተራ ድምጽ ብልጫ ሳይሆን ሊሻሻል የሚችለው በተጠናከረ አብላጭነት ወይም በውሳኔ ህዝብ ብቻ ነው ማለት ነው::የጸረ ዲሞክራሲያዊና ፈላጭ ቆራጭ ህገመንግሥታት አንዱ መለዩ እንዲያውም እዚህ ላይ ነው:: ፈላጭ ቆራጭ ገዥዎች በቻቸውን ያጸደቁትን ህገመንግሥታቸውን ህብረተሰቡ ተረባርቦ እንኳን ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው በማይችለው ሁኔታ ይቀለልፋታል:: የኢህአዴግ ህገመንግሥት ከዚህ የተለየ አይደለም:: የአጸዳደቁ ሂደት ሰነዱን የአንድ እፍኝ አናሳ ኃይል የፖለቲካ ፕሮግራም አድርጉታል:: በሌላ በኩል ደግሞ ወሳኝ በሆኑ ጥያቄዎች ላይ ከህዝቡ 5 ከመቶ እንኳን የማይሆኑ ክፍሎች በተሰጣቸው የቬቶ መብት ምክንያት ምንም ዓይነት መሻሻል እንዳይደረግ ሊያግዱ የሚችሉበት ሁኔታ አለ::

7ኛ/ የብሄርና ብሄረሰቦች መብት ይረጋገጥ

አንድ ህገ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሁኔታ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የሚያረጋግጠውና ብሄሮች በዚህ የጋራ ህገመንግሥት ጥላ ሥር እየተጠናከረ በሚሄድ የአንድነትና የወንድማማችነት መንፈስ ከሆነ እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ብሄሮች፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች በገዛ ጉዳያቸው ባለቤትነታቸው፣ የጋራ በሆነ የአገር ጉዳይ ተገቢ ተሳትፎቸው በህገመንግሥቱ መረጋገጡ ብቻ ነው:: ይህም ማለት በአንድ በኩል በአጠቃላዩ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ክልል ውስጥ የአስተዳደርና የፖለቲካ አወቃቀራቸውን ራሳቸው የመወሰን፣ የሰብአዊም ሆነ የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነታቸው ተረጋግጦ ይህንን በመሰላቸው ኢኮኖሚም ሆነ ማህበራዊ ፖሊሲ መሠረት ከጥቅም ላይ የማዋል መብታቸው እንዲረጋገጥ ይጠይቃል:: በሌላ በኩል ደግሞ የጋራ የሆኑ የሃገር ጉዳዮች ሲወሰኑ በዚህ የውሳኔ ሂደት ተገቢ ተሳትፎቸው መረጋገጥ አለበት:: የኢህአዴግ ህገመንግሥት የብሄር ብሄረሰቦችን መብት እስከመገንጠል አውቃለሁ ይበል እንጂ በገዛ ጉዳያቸው የራሳቸውን እድል በራሳቸው እንዲወስኑ አይፈቅድላቸውም:: የብሄር ብሄረሰቦችን በአገር የጋራ ጉዳይ ለማረጋገጥ ፌዴሬሽን አቋቁሙ ይበል እንጂ የፌዴሬሽኑ ምክርቤት በህግ ማውጣት ሂደት እንዲሳተፍ አይፈቅድም::

* * *

ከፍ ብለን በተደጋጋሚ እንዳልነው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ነጻ ምርጫን እውን አርጎ የሚያውቅበት ወቅት በታሪካችን አልታየም:: የሽግግር ዘመን የተባለውም በኢህአዴግ ሥር የተካሄዱት ምርጫዎች የዘረዘርናቸውን ዓለም አቀፍ የነጻ፣ ርአታዊና ሃቀኛ ምርጫዎች መለኪያዎች ተሟልተው ተካሄደዋል ካልተባለ በስተቀር በዚህ አንጻር ሃገሪቱን አንዲትም ርምጃ ወደፊት ሳያራምድ አስተሟል:: በዴሞክራሲያዊ ህገ መንግሥትም አንጻር ኢትዮጵያ በታሪኳ እንዲህ ዓይነት ዕድል አታውቅም:: የሽግግር ዘመን የተባለውም የኢህአዴግ ህገ መንግሥት/ፕሮግራም የዴሞክራሲያዊ ህገ መንግሥትን መርሆዎች ያካተተ ነው ተብሎ እስካልተቀጠፈ ድረስ ዛሬም ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት የላትም::

ስለሆነም አዲስ ዴሞክራሲያዊ ጅማሮ ብለን ስንጠይቅና ለዚህም በጋራ ለመታገል ቆርጠን ስንነሳ ማንም ቢሆን የቅንጠት፣ የሥልጣን ሽሚያና "የማይመስል ነገር" እንደጠየቅን አርጎ ሊወስዱብን አይቻልም:: ያለ ነጻ ምርጫ በየትም ዓለም ማንም ህዝብ ፍላጎቱንና ዓላማውን የሚያንጸባርቅበት ዘዴ እንደሌለ ሁሉ በኢትዮጵያም ያለዚህ ዴሞክራሲያዊ ሂደት የህዝቡ ፍላጎት የሚገለጽበት ዘዴ አይኖርም:: ያለ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት ማንም ህዝብ የህግ የበላይነትን አንገስ በሰላም፣ በዴሞክራሲያዊና በተረጋጋ ሁኔታ የተሻለ ህይዎት ገንብቶ አያውቅምና ለኢትዮጵያም ህዝብ የተረጋጋ ኑሮ ከህግ የበላይነት ሥርዓት በስተቀር ሌላ ዘዴ አይኖርም::

አዲስ ዴሞክራሲያዊ ጅማሮ ብለን ሡሡሡ ስንጠይቅና ለዚህም በጋራ ለመታገል ቆርጠን ስንነሳ፣ ከላይ የዘረዘርናቸው የነጻ ምርጫና የዴሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት እንዲሟሉ እንታገላለን ስንል እንደገና "ሌላ" ሽግግር መጠየቃችን አይደለም::ሽግግር አልተደረገም:: ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ለሃገራችን ያስፈልጋል ማለታችን ነው:: ይህንንም አሌ የሚሉ ሃይሎች ካሉ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተካሄዷል:: በኢትዮጵያ በዴሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት አማካኝነት የህግ የበላይነት ተረጋግጧል ብለው በሬ ወለደ ሊያሳምኑን ይገባል:: ይህ አልተደረገም ካሉ ደግሞ ከነጻ ምርጫና ከዴሞክራሲያዊ ህገመንግሥት ሌላ ምን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመሸጋገሪያ መንገድ እንዳለ ሊጠቁሙን ይገባል::

እና በበኩላችን ከዚህ ሌላ መፍትሄ የለም እንላለን:: እና ብቻ ሳንሆን በሃገሪቱ ያሉ ዴሞክራሲያዊ የሆኑ ሃይሎች ሁሉ የመረጡትን ድርጅት በመርጡ፣ የመረጡትንም የትግል ስልት በመርጡ፣ ያሻቸውን የትግል ታክቲክና ስትራቴጂ ቢቀይሱ ትግሉ የኢትዮጵያ ህዝብ የገዛ እድሉ ወሳኝ የሚሆንበትን መድረክ ለማመቻቸት እንጂ አንዱን ጸረ ዴሞክራቲክ አገዛዝ በሌላ በማይሻል ፈላጭ ቆራጭ ኃይል ለመተካት እስካልሆነ ድረስ በዚህ የጋራ ትግል መድረክ አብረውን ሊቆሙ ይገባል እንላለን:: በዚህ ግልጽ በሆነ ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ዓላማ ያምኑ እንደሆን በሆነ ባልሆነው ሰበብ የህዝቡን ትግል ግራ ከማጋባት፣ ለፈላጭ ቆራጩ ኃይል አላስፈላጊ ጪጪጪ ፋታ ከመስጠትና የህዝባችንን የመከራ ዘመን ከማራዘም ይልቅ በዚህ አነስተኛ መድረክ ላይ አብረን ተሰልፈን እንድንታገል ጥሪ እናደርግላቸዋለን:: ይህንን የማይቀበሉ ከሆነ ደግሞ የዴሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ኃይሎች ጪጪጪጪጪ የትግል አንድነት በምን ሌላ አነስተኛ መድረክ ላይኛ በምን ሌላ ህዝባዊ ዓላማ ላይ ሊገነባ እንደሚችል ለኛም ለኢትዮጵያ ህዝብም በግልጽ ማስታወቅ ይኖርባቸዋል::